የዘር አቆጣጠር ለማታውቁ

ሰላምታዬ ይድረሳችሁ

የዘር አቆጣጠር ለማታውቁ ፣ ልጅ ፣ አባት ፣ አያት ፣ ቅድመ-አያት ፣ ቅም-አያት ፣ ቅማንት፣ ሽማት ፣ምንዥላት ፣ አንጅላት፣ ፍናጅ፣ ቅናጅ ፣አስልጥ ፣ አምስጥ ፣ ማንትቤ፣ ደርባቴ ፣፣ ይባላሉ :: ምናልባት በጊዜው አስገዳጅነት መጠቀም ካለብኝ ብዬ በግጥም መልክ ለመጻፍ ሞከሬ ፣ ስኩ ፣ የሳተውን ግጥሜን ጀባ ልበላችሁ ::

የኔ ትውልድ የዘር ቆጠራ

አያልፍም ነበር ካያቶቹ ተራ

የዛሬዎቹ ብልህ ናቸው

ከአዳም መለስ መቅረባቸው

ቅድመ አያት ፣ ቅም አያት

ቅማንት ፣ ሽማት ፣ አንጅላት

አናውቅም ነበር የተሃድሶ ጥራት

ፍናጅ ፣ቅናጅ፣ አስልጥ ፣ አምስጥ

ድሮ አልነበረም ወደ ጀሮ የሚሰምጥ

ማንትቤ ፣ ደርባቴ ብሎ ነገር

አናውቅም ነበር ዘልቆ መካረር

ከአዳም ወዲህ መጀመሩ

ምን ሊፈይድ ለነገሩ

ቦታ አስፍቶ በትንሣዔ

ካልጠፋ ቀን ለጉባዔ

ሁሉም ሕልም ከጀርባዬ

ከሰላምታ ጋር

ብስራት